# በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ፍልሰተኞችን እና ስደተኞችን ይዞ ወይም አስሮ ማቆየትን (detension) እንዲሁም ጠርዞ ወደሀገራቸው መመለስን (deportation) የሚመለከት ሥዕላዊ መግለጫ

በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ፤
https://www.scalabrini.org.za/detentiondeportation/

## በደቡብ አፍሪካ ስደተኞችን ጠርዞ የመመለሱ ሂደት ምን ይመስላል?

ለተጨማሪ መረጃ በሚቀጥለው ገጽ የተቀመጡትን በተደጋጋሚ የሚነሡ ጥያቄዎችን (FAQs) ይመልከቱ

በደቡብ አፍሪካ ታስራችሁ ወይም ተይዛችሁ ከቆያችሁ የሕግ ባለሙያዎችን ዕርዳታ እንድታገኙ **አጥብቀን** እንመክራለን።

ይህ ደግሞ ይበልጥ ጠቃሚ የሚሆነው በተያዛችሁ በ48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድቤት ከቀረባችሁ ነው። በሚቀጥለው ገጽ በመጠይቅ ቁጥር 8 የተቀመጠውን ይመልከቱ

የጥገኝነት ጥያቄ ካመለከታችሁ (ወደሀገራችሁ ብትላኩ የመጠቃትና የመሳደድ አደጋ ስለሚገጥማችሁ) ተጠርዛችሁ ወደ ሀገርቤት ልትላኩ አይገባም። በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በአስቸኳይ የሕግ ባለሙያዎችን እርዳታ ያግኙ።

### ደረጃ አንድ

ማንነታችሁን እንድትገልጹ ሊጠይቋችሁ የሚችሉት የፖሊስ መኮንን ወይም የፍልሰተኞች ጉዳዮች መኮንን (Immigration Officer) ብቻ ናቸው። እነዚህ የሕግ አካላት በሕጋዊ መንገድ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ መቆየት እንደማትችሉ ሊያደርጋቸው የሚችል «ምክንያታዊ ጥርጣሬ» ካላቸው፣ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እስከ 48 ሰዓታት ድረስ ይዘው ወይም አስረው ሊያቆይዋችሁ ይችላሉ። በእነዚህ ሰዓታት ውስጥ ማንነታችሁንና በደቡብ አፍሪካ ያላችሁብትን ሁኔታ ማጣራት አለባቸው። የሕግ ባለሞያዎችን እርዳታ ያግኙ።

### ደረጃ ሁለት

«ሕገወጥ የውጪ ዜጎች» ብሎ ሊበይናችሁ የሚችለው የፍልሰተኞች ጉዳዮች መኮንን (Immigration Officer) ብቻ ነው። ይህ ከሆነ በኋላ ተጠርዞ ወደሀገርቤት የመመለሱ ሂደት ይጀምራል። ጉዳዩ በምትረዱት ቋንቋ፣ በጽሑፍ ሊቀርብላችሁ እና እንድታውቁት ሊደረግ ይገባል። ይህንን ውሳኔ የማስቀልበስ መብት እንዳላችሁም ሊነገራችሁ ይገባል። ይህ ከሆነ በኋላ የየፍልሰተኞች ጉዳዮች መኮንኖች ወደሀገራችሁ ጠርዘው ለመመለስ እንዲያስችላቸው ይዘው ወይም አስረው የማቆየት መብት አላቸው፤ ይህ የእነሱ ሥልጣን ነው።

### ደረጃ ሦስት

በታሰሩ ወይም ወደማቆያ ማቆያ በገቡ በ48 ሰዓታት ውስጥ ያሰሮት የሕግ አካል በአካል ፍርድቤት ሊያቀርብዎት ይገባል። ተይዘው ወይም ታስረው ይቆዩ ወይም ይለቀቁ የሚለውን ብያኔ የሚሰጠው ፍርድቤቱ ነው። የፍርድቤቱ ውሳኔ በጽሑፍ ሊሰጥዎ ይገባል። በዚሁ መሰረት ፍርድቤቱ ተይዘው ወይም ታስረው የሚቆዩበትን ጊዜ እስከ 30 ቀናት ማራዘም ይችላል።

### ደረጃ አራት

የመጀመሪያዎቹ 30 ቀናት ሲጠናቀቁ የፍልሰተኞች ጉዳዮች መኮንን ተይዘው ወይም ታስረው የሚቆዩበትን ጊዜ በ30 ቀናት ያህል እንዲራዘምለት ሊጠይቅ ይችላል። እርስዎም በአካል ፍርድቤት ሊገኙ ወይም በጽሑፍ ሌላ ሰው ሊወክሉ ይችላሉ። ሆኖም የፍልሰተኞች ጉዳዮች መኮንኑ ማመልከቻ በአንድ ውሳኔ ሊራዘምለት የሚችለው ጊዜ ለ30 ቀናት ብቻ ነው። ፍርድቤቱ ተይዘው ወይም ታስረው የሚቆዩበት ቀን እንዲራዘም ሊፈቅድ የሚችለው አሳማኝ ምክንያት ካለው ብቻ ነው። ይህም ሆኖ ተይዘው ወይም ታስረው ሊቆዩ የሚችሉት አጠቃላይ ቀናት 120 ብቻ ናቸው።

### ደረጃ አምስት

ተጠርዘው ወደሀገርቤት የመላክዎ ጉዳይ እርግጥ ከሆነ፣ በሐውተንግ አውራጃ ውስጥ ወደሚገኘው ሊንዴላ ፍልሰተኞችን ይዞ ወይም አስሮ ማቆያ ጣቢያ ሊዛወሩ ይችላሉ። ይህን ለመተግበር አስቸጋሪ ስለሆነ ወደ ሊንዴላ ጣቢያ እስኪላኩ ወይም በቀጥታ ወደሀገርቤት ተጠርዘው እስኪመለሱ ድረስ በፖሊስ ጣቢያ ወይም በእስርቤት ሊቆዩ ይችላሉ። ተይዘው ወይም ታስረው በሚቆዩባቸው ጣቢያዎች በርካታ መብቶች ቢኖርዎትም (በሚቀጥለው ገጽ ያለውን ይመልከቱ) በሊንዴላና መሰል ማቆያዎች ውስጥ ያለው ሁኔታ ጥሩ እንዳልሆነ ሊያውቁት ይገባል።

### ደረጃ ስድስት

የደቡብ አፍሪካ የሀገር ውስጥ ጉዳዮች መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) ተጠርዘው ወደሀገርቤት የሚመለሱበትን ሁኔታ ለማቀናጀት ከሀገርዎ የቆንጽላ ጽሕፈት ቤት፣ ኢምባሲ፣ ወይም የፍልሰተኞች ጉዳይ መኮንኖች ጋር ይነጋገራል። ተጠርዘው ወደሀገርዎ በሚመለሱበት ጊዜ የሚመለከተው የመንግሥት አካል ተቀብሎ እንደሚያስተናግድዎ እርግጠኛ መሆን መቻል አለባቸው።

### ደረጃ ሰባት

ተጠርዘው ወደሀገርቤት ከመመለስዎ በፊት፣ ስለጉዳዩ ወዲያውኑ እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል። ከዚያ በኋላ በአውቶቡስ፣ በባቡር፣ ወይም በአውሮፕላን ተጠርዘው ወደሀገርቤት ሊመለሱ ይችላሉ። ተጠርዘው ወደሀገርቤት ከተመለሱ በኋላ በቀጣይ አምስት ዓመታት ውስጥ ወደ ደቡብ አፍሪካ ከመግባት የመታገድ ዕድልዎ ከፍተኛ ነው። ከእነዚህ አምስት ዓመታት በኋላም ቢሆን እግዱ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመግባት የሚያስፈልግዎን ቪዛ የማግኘት ዕድልዎን ሊያጨናግፍ ይችላል።

ወደ ሀገርቤት ተጠርዘው ለመመለስ ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ የገንዘብ ዐቅም እስካለዎ እና ወደሀገርቤት ለመመለስ የሚያስፈልጉ ሰነዶች እንዳለዎት እስካረጋገጡ ድረስ፣ ደቡብ አፍሪካን የመልቀቅ ሂደትዎን በግልዎ ሊያቀናጁት ይችላሉ። በዚህ መልኩ ስኬታማ ከሆኑ፣ ሂደቱን ለደቡብ አፍሪካ የሀገር ውስጥ ጉዳይ መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) በተከታታይ ሪፖርት የሚያደርጉበት ቅጽ (ፎርም) ይሰጥዎታል። አደጋ ላይ እስካልጣልዎ ድረስ ከደቡብ አፍሪካ የመውጣት ሂደትዎትን በራስዎ ማቀናጀት የሚችሉበትን አጋጣሚ በእጅጉ እናበረታታለን።

በታሰሩ ወይም ተይዘው በቆዩባቸው ቀናት ውስጥ ተጠርዘው ወደሀገርዎ ካልተመለሱ የመለቀቅ መብት እንዳለዎት ያስታውሱ። ይህ ጉዳይ የሚመለከታቸው ድርጅቶችን ለማግኘት ወይም ለማነጋገር የሚቀጥለውን ገጽ ይመልከቱ።

## ፩፤ አንድ ሰው ከሰነድ ወይም ዶክመንት ጋር በተያያዘ ሊታሰር ወይም ተይዞ ሊቆይ የሚችለው መቼ ነው?

በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ወረቀትዎን ወይም የመታወቂያ ሰነድዎን መጠየቅ የሚፈቀድላቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የፍልሰተኞች ጉዳዮች መኮንን (ኢሚግሬሽን ኦፊሰር) ብቻ ናቸው። ወረቀትዎ ወይም የመታወቂያ ሰነድዎ ስምዎንና ፎቶግራፍዎን ጭምር የያዘ ማንነትዎን የሚገልጽ መሆን አለበት። የፖሊስ መኮንኖች ወይም የፍልሰተኞች ጉዳይ መኮንኖች ሊያስሩዎ ወይም ይዘው ሊያቆይዎ የሚችሉት በሕጋዊ መንገድ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ መቆየት እንደማትችሉ ሊያሳምናቸው የሚችል «ምክንያታዊ ጥርጣሬ» ካላቸው ብቻ ነው።

## ፪፤ ደቡብ አፍሪካዊ እንዳለመሆኔ መጠን፣ ምን ዓይነት ሰነድ ይዤ ነው መንቀሳቀስ የሚገባኝ?

ፓስፖርትዎ ላይ ቪዛ ከተመታልዎ፣ ቢያንስ እውነተኝነቱ የተረጋገጠ (ሰርቲፋይድ) የፓስፖርትና የቪዛ ቅጂ (ኮፒ) ሁልጊዜም ይዘው ሊንቀሳቀሱ ይገባል። የስደተኝነት ማረጋገጫ (ሪፊውጂ ስታተስ) ከተሰጥዎትም፣ እውነተኛነቱ የተረጋገጠውን የሰነዱን ቅጂ (ኮፒ) ሁልጊዜም ይዘው ሊንቀሳቀሱ ይገባል። ያለዎት ሰነድ የጥገኝነት መጠየቂያ ጊዜያዊ ወረቀት (አሳይለም ሲከር ቴምፖራሪ ፐርሚት) ከሆነ ግን ሁልጊዜም ዋናውን ወረቀት (ኦሪጅናል ዶክመንት) ይዘው ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

## ፫፤ ወደሀገርቤት ተጠርዤ የምመለስ ከሆነ፣ ልታሰር ወይም ተይዤ ልቆይ የሚገባኝ የት ነው?

ሊታሰሩ ወይም ተይዘው ሊቆዩ የሚችሉት የደቡብ አፍሪካ የሀገር ውስጥ ጉዳይ መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) ዳይሬክተር ጀነራል በለያቸው ቦታዎች ውስጥ ብቻ ነው (ይህም በመንግሥት ጋዜጣ – Government Gazette ታትሟል)። እነዚህ ቦታዎች አንዳንድ የፖሊስ ጣቢያዎችን፣ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ጉዳይ መሥሪያቤት በዋናነት ወይም በወኪልነት የሚያስተዳድራቸው የማቆያ ሥፍራዎችንና ቢሮዎችን ይጨምራሉ። ተጠርዘው ወደሀገርቤት ሊላኩ የሚጠባበቁ ሰዎች፣ ብዙውን ጊዜ በሐውተንግ አውራጃ ወደሚገኘውና በደቡብ አፍሪካ ብቸኛ የፍልሰተኞች ማቆያ ወደሆነው የሊንዴላ ማዕከል እንዲዛወሩ ይደረጋል።

## ፬፤ በመታሰሪያ ወይም ተይዞ መቆያ ሥፍራዎች ውስጥ ያለኝ መብት ምንድነው?

በመታሰሪያ ወይም ተይዞ መቆያ ሥፍራዎች ውስጥ ያሉዎት መብቶች የሚከተለው ናቸው፤ (፩) የታሰሩበትን ወይም ተይዘው ወደመቆያ የተወሰዱበትን ምክንያት እንዲሁም በማቆያ ቦታ ውስጥ ስላለዎት መብት የማወቅ መብት። (፪) የሰውን ልጅ ክብርና የሰብዓዊ መብትን ዝቅተኛ ደረጃ በሚያሙላ ሁኔታ ውስጥ የመቆየት መብት፤ እነዚህም በቂ የማረፊያ ቦታ፣ ምግብ፣ የሚነበቡ መጻሕፍት (reading materials) እና የሕክምና አገልግሎትን ይጨምራሉ። (፫) በፍላጎትዎ መሰረት የሕግ ባለሙያ የመምረጥና የማማከር መብት፣ ወይም በመንግሥት ወጪ የሕግ አማካሪ እንዲመደብልዎ የመጠየቅ መብት (፬) በባለቤትዎ፣ በትዳር አጋርዎ ወይም ዘመድዎ የመጎብኘት መብት እንዲሁም በሀይማኖት አባት ወይም አማካሪ እና በሕክምና ባለሙያዎች የመጎብኘት መብት (፭) በወንጀል ከሚጠረጠሩ ሰዎች ተለይቶ የመቆየት መብት

## ፭፤ በማቆያ ሥፍራዎች ውስጥ እንዴት ነው የሕግ እርዳታ ለማግኘት የምችለው?

ከታሰሩ ወይም ወደማቆያ ሥፍራ ከተወሰዱ በኋላ የሕግ እርዳታ እንዲያገኙ አጥብቀን እንመክራለን። በማቆያ ሥፍራ ውስጥ በባለቤትዎ ወይም በትዳር አጋርዎ እንዲሁም በቤተዘመድዎ የመጎብኘት መብት አለዎት። በመረጡት የሃይማኖት አማካሪ የመጎብኘት መብትዎም የተጠበቀ ነው፤ ይህም የሕግ አማካሪ እንዲያገኙ ይረዳዎታል። የሕግ ባለሞያ ለመቅጠር ዐቅም ከሌለዎ ደግሞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ሊያገኙ ወይም ሊያማክሩ ይችላሉ። (ማስታወሻ፤ የታሰሩት በወንጀል ጉዳይ ቢሆንም እንኳን የሕግ ድጋፍ መጠየቅ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል።)

## ፮፤ ተጠርዞ ወደሀገርቤት ሊመለስ የማይችለው ማነው?

በፍልሰተኞች ድንጋጌ (ኢሚግሬሽን አክት) መሰረት ጥገኝነት ጠያቂዎች እና ስደተኞች (ሪፍዩጂስ) ወደሀገራቸው ለመመለስ ላይታሰሩ ወይም ተይዘው ላይቆዩ ይችላሉ፤ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ዓለምአቀፍ የጥገኛ ጠያቂዎችን ወደሀገራቸው ያለመመለስ ድንጋጌን (non-refoulement) መጣስ ያህል ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው። ይህ ዓለምአቀፍ ድንጋጌ ተቀባይ ሀገራት ጥገኝነት ጠያቂዎች የመጠቃትና የመገደል ዓይነተኛ አደጋ ሊያጋጥማቸው ወደሚችልባቸው ሀገራት ሊመለሱ አይገባም ይላል። ይህ ድንጋጌ ጥገኝነት የመጠየቅ እቅድ ያላቸውን ሰዎች ያካትታል። ሆኖም፣ የጥገኝነት ጥያቄያቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ውድቅ የተደረገባቸው እና ይህንኑ ውሳኔ ለመቀልበስ ግፊት ያላደረጉ ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ለመታሰርና ተጠርዞ ወደሀገርቤት ለመመለስ አደጋ የተጋለጡ ናቸው። የመጨረሻው አማራጭ ካልሆነ በስተቀር፣ ልጆች (እድሜያቸው ከዐሥራስምንት ዓመት በታች የሆነ) ሊታሰሩ ወይም ተይዘው ሊቆዩ አይገባም። የመጨረሻው አማራጭ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ልጆች ለአላስፈላጊ እንግልት እንዳይዳረጉ የሚያስፈልገው ጥንቃቄና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል።

## ፯፤ ጠርዞ ወደሀገርቤት የመመለሱ ሥርዓት በተግባር ምን ይመስላል?

የደቡብ አፍሪካ የሀገርውስጥ ጉዳይ መሥሪያቤት (Department of Home Affairs) በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ጠርዞ ወደሀገርቤት ይመልሳል። በሕግ የተደነገጉ ሊሟሉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎችና ጥበቃዎች ቢኖሩም በሊንዴላ የማቆያ ጣቢያ የሚገኙ በርካታ ታሳሪዎች (ዲቴይኒስ) በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነው የሚገኙት። በጣቢያው የሚቆዩ ሰዎች ከሕግ አግባብ ውጪ ከ120 ቀናት በላይ የሚቆዩ መሆኑ ታውቋል። የጣቢያው ሁኔታም የከፋ ነው፤ ይህም የጤና አገልግሎት ውስን መሆንን፣ የሕግ አማካሪ ማነስን፣ እንዲሁም ጥገኛ ጠያቂዎችንና ልጆችን በሕገወጥ መንገድ ይዞ ማቆየትን ይጨምራል።

## ፰፤ ዕርዳታ ያስፈልገኛል፣ ማንን ላግኝ ወይም ላማክር ?

Scalabrini Centre of Cape Town
WWW.SCALABRINI.ORG.ZA

SONKE GENDER JUSTICE
HIV/AIDS • GENDER EQUALITY • HUMAN RIGHTS
WWW.GENDERJUSTICE.ORG.ZA

የሰብዓዊ መብት ጠበቃዎች ፤ | መሲና፤ 015 534 2203
ደርባን፤ 031 301 0531 |
ፕሪቶሪያ፤ 012 320 2943
ጆሐንስበርግ፤ 011 3391960
በኬፕታውን ዩኒቨርሲቲ የስደተኞች መብት ተሟጋች፤| 021 650 5581
በኬፕታውን ከተማ የስካሊብሪኒ ማዕከል፤ | 021 465 6433